## ማድረግ የምትችሉት

1. **ምልክቶቹን ዕወቁ፡፡** የኪስ ቦርሳ ውስጥ የሚገቡትን በ17 ቋንቋዎች ቁልፍ ምልክቶችን የሚገልጹትን መጠቆሚያ ካርዶቻችንን እዘዙ፡፡ እነዚህን ካርዶች በአካባቢያችሁ መበተን ትችላላችሁ፡፡ በተለይ ለፈጥኖ ደራሾችና ለጤና ባለሙያዎችም መጠቆሚያ ካርዶች አዘጋጅተናል፡፡ በይበልጥ ለመረዳት፡- www.dhs.gov/Bluecampaign

2. **ምልክት ስታዩ ጠቁሙ፡፡** የሕገወጥ ሰው ዝውውር ተጠቂ የሚመስላችሁ ሰው ስታገኙ ወይም ሕግ አስከባሪ ከሆናችሁና በአካባቢያችሁ ያለውን HSI መገናኘት ከፈለጋችሁ የ HSI መጠቆሚያ መስመር ላይ ደውሉ፡-

    - **(866) 347-2423** (ከዩ ኤስ እና ከካናዳ ነጻ)
    - **(802) 872-6199** (ከየትኛውም ዓለም ነጻ ያልሆነ)
    - ወይም ምልክቶችን በድህረ ገጽ አድራሻ www.ice.gov/tips ላይ ጠቁሙ (ከየትም ኢንተርኔት ከሚገኝበት ቦታ)

    ከፍተኛ ስልጠና ያላቸው ሕግ አስከባሪ ባለሙያዎች የሰው ዝውውር ጥቆማ ለመቀበልና በአገርና በዓለም ዙሪያ በሥራ ላይ ላሉ የሕገወጥ ሰው አዘዋዋሪ መርማሪዎች መረጃ ለማሰራጨት በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀን ይገኛሉ፡፡ ስምን ሳይገልጹ በድብቅ ጥቆማ ለማድረግ በኢንተርኔት ላይ የሚገኘውን ቅጽ መሙላት ወይም በነጻ መጠቆሚያ መስመር ላይ መደወል ይቻላል፡፡

    **ብሔራዊ የሕገወጥ ሰው ዝውውር መረጃ ማዕከል (National Human Trafficking Resource Center (NHTRC)) ጋር በስልክ ቁጥር 1-888-373-7888 በመደወል የሚከተለውን ማድረግ ትችላላችሁ፡-**

    - እርዳታ ማግኘትና አካባቢያችሁ የሚገኝ አገልግሎት ሰጪ ጋር መገናኘት፤
    - ሕገወጥ የሰው ዝውውር ሲካሄድ መረጃ መስጠት፤ ወይም
    - ስልጠና፣ ቴክኒካዊ እርዳታ ወይም ሌላ ነገር በመጠየቅ በይበልጥ መረዳት፡፡

    NHTRC ከየትም ከአገር ውስጥ የሚመጡ ጥሪዎችን በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀን፣ በዓመት በእያንዳንዱ ቀን የሚቀበል ብሔራዊ የነጻ ስልክ መስመር ነው፡፡ NHTRC ሕግ አስከባሪ ወይም የኢሚግሬሽን ሥልጣን አይደለም፣ የሚተዳደረውም መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት ነው፡፡

3. **በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የአገር ውስጥ ደህንነት ምርመራዎች (Homeland Security Investigations (HSI)) እወቁ፡፡** የHSI መጠቆሚያ መስመር ጋር በመደወል በአካባቢያችሁ የሰው ዝውውር ጉዳዮችን የሚያስተናግዱ የHSI ልዩ ተወካዮችና የተጠቂ እርዳታ ባለሙያዎችን (HSI Special Agents and Victim Assistance Specialists) በመገናኘት በጋራ የሚመረመር ጉዳይ ከመኖሩ እንኳን በፊት ግንኙነት መፍጠር ትችላላችሁ፡፡ መፍትሄ ለማምጣት መረጃ በማካፈል ተባበሩ፡፡

4. **በአካባቢያችሁ የሚገኘውን የሥራ ኃይል ተዋወቁ፡፡** ሕገወጥ የሰው ዝውውር የሥራ ኃይሎች የፌዴራል፣ የስቴት፣ የአካባቢው፣ የካውንቲው እና የጎሳ ሕግ አስከባሪ እና የዓቃቤ ሕግ እንዲሁም የተጠቂ አገልግሎቶች የሚሰጡ NGOዎችን ያጠቃልላሉ፡፡ አካባቢያችሁ የሕገወጥ ሰው ዝውውር ሥራ ኃይል (Human Trafficking Task Force) መኖሩን ለማወቅ www.bja.govን ጎብኙ፡፡ ካለ ግንኙነት ፈጠሩና በጥረቶቻቸው ተካፈሉ፡፡

5. **እራሳችሁንና የሥራ ባልደረቦቻችሁን አስተምሩ፡፡** ሕግ አስከባሪ ከሆናችሁ በኮምፒዩተር የምንሰጠው አሳታፊ ነጻ ሥልጠና የተለያዩ የቃለመጠይቅና የምርመራ ስልቶች በማቅረብ በይበልጥ ብቃት እንዲኖራችሁ ይረዳል፡፡ የሚከተለውን ድህረ ገጽ ጎብኙ፡- www.fletc.gov/training/programs/human-trafficking-training-program፡፡ ፈጥኖ ደራሽ ከሆናችሁ ወይም የጤና ባለሙያ ከሆናችሁ በኢንተርኔት የምንሰጠውን አጠቃላይ አሳታፊ ሥልጠና ውሰዱና የፈጥኖ ደራሽ ቪዲዮዋችንን ተመልከቱ፡፡ የሚከተለውን ጎብኙ፡- www.dhs.gov/Bluecampaign፡፡

6. **የ Blue Campaign ድህረ ገጽን ጎብኙ፡፡** ተጨማሪ ሥልጠና፣ የመረጃ ማካፈያ መጽሔቶች፣ የተጠቂ እርዳታ መጽሔቶች እና ሕገወጥ የሰው ዝውውርን ለማቆም በሚደረገው ትግል ለመሳተፍ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ድህረ ገጽ ጎብኙ፡- www.dhs.gov/Bluecampaign፡፡ ፌስቡክ ላይ በሚከተለው ገጽ "Like" አድርጉን፡- www.facebook.com/bluecampaign፡፡ ወይም በሚከተለው ኢሜል ጻፉልን BlueCampaign@hq.dhs.gov፡፡

ተጠቂዎችን መለየት

ሕግ አስከባሪዎች፣ ፈጥኖ ደራሾች እና የጤና ባለሙያዎች



# ምን ማድረግ ትችላላችሁ?

*በሕገወጥ የሰው ዝውውር የተጠቁ ሰዎችን መለየት መቻልና መጠቆም*

BLUE CAMPAIGN

One Voice. One Mission. End Human Trafficking.

# ምን ማድረግ ትችላላችሁ?

*በሕገወጥ የሰው ዝውውር የተጠቁ ሰዎችን መለየት መቻልና መጠቆም*

## ተጠቂዎች ፊትለፊት ናቸው

ሥራ ላይ ባላችሁበት ወቅት የሰው ዝውውር ተጠቂ ሊያጋጥማችሁ ይችላል። የሰው ዝውውር ተጠቂዎች በማህበረሰቦቻችን ውስጥ አሉ። የቤት ውስጥ ጥቃት ተፈጻሚ ሕግ አስከባሪዎች በሚጠሩበት ወቅት፣ በማሳጅ ቦታ፣ በባር እና በስትሪፕ ክለብ ውስጥ አንድ ክር ተፈጥሮ በሚጠሩበት ወቅት ወይም ፖሊስ መንገድ ላይ መኪና በሚያስቆሙበት ወቅት የሰው ዝውውር ተጠቂ ሊያጋጥማቸው ይችላል። ፈጥኖ ደራሾችና የጤና ባለሙያዎች ለድንገተኛ ሁኔታ ምላሽ በሚሰጡበት ወቅት ወይም ታካሚዎችን በሆስፒታል ወይም በዶክተር ቢሮ በሚያዩበት ወቅት አንዳንድ ምልክቶች ሊያስተውሉ ይችላሉ። የጤናና የደህንነት ተቆጣጣሪዎች በሬስቶራንቶች፣ በፋብሪካዎች፣ በግንባታ ሳይቶች ወይም በእርሻዎች ላይ ተጠቂዎች ሊያገኙ ይችላሉ።

## የዝውውር ተጠቂዎች ማንኛውም ዕድሜ፣ ዘር፣ ጾታ ወይም ዜግነት፣ የአሜሪካ ዜጎችን ጨምሮ ሊሆኑ ይችላሉ።

በአገር ውስጥ የኑሮ ሁኔታቸው ሕጋዊ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ተጠቂዎች ሕጋዊም ሕገወጥም የሥራ ረድፍ ውስጥ ተሰማርተው ይገኛሉ፤ አንዳንዶቹ በውሸት ጥሩ ክፍያ ያለው ሥራ ታገኛላችሁ ተብለው ወይም በፍቅር ተታልለው ይገባሉ። ብዙውን ጊዜ በቤት ውስጥ አገልግሎት፣ በእርሻ ወይም ፋብሪካ ሥራ ወይም ሌሎች ዓይነቶች የግዴታ ሥራ ወይም ጋለሞተኝነት ላይ ይሰማራሉ። በፌዴራል ሕግ መሠረት ከሕጋዊ ዕድሜ በታች ያሉ ጋለሞታ ሆነው የሚገኙ ወጣቶች የሰው ዝውውር ተጠቂዎች ናቸው።

## ሰው አዘዋዋሪዎች እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ

ሰው አዘዋዋሪዎች የሚያደቡት ብዙም ማህበራዊ ድጋፍ የሌላቸው ሰዎች ላይ ነው። የገንዘብ ችግር ያለባቸው፣ ቤት ውስጥ ጥቃት የሚደርስባቸው፣ የተፈጥሮ ቀውስ ወይም የፖለቲካ አለመረጋጋት ተጠቂዎች ወይም በተለያየ ምክንያት ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን ይፈልጋሉ። አዘዋዋሪዎች ተጠቂዎችን ለማጥመድ የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀማሉ፣ ማጥቃትን ወይም የአእምሮ ተጽዕኖን ጨምሮ። ስነልቦናዊ ጠባሳው ጥልቅ ከመሆኑ የተነሳ ብዙዎቹ እራሳቸውን እንደ ተጠቂ ላያዩ ወይም እርዳታ ላይጠይቁ ይችላሉ፣ በግላጭ ሕዝብ ያለበት ቦታ ላይ ቢሆኑም።

## የሕገወጥ ሰው ዝውውር ምልክቶች

ቁልፍ ምልክቶችን ማወቅ መቻል ሕይወት ሊያድን ይችላል። ይህ ተጠቂዎችን ለመለየት የመጀመሪያው እርምጃ ነው። ከዚህ በታች የተጠቀሱት ምልክቶች በሙሉ እያንዳንዱ የሰው ዝውውር ሁኔታ ላይ ላይከሰቱ ይችላሉ። የአንድ ምልክት መኖር ወይም አለመኖር የሰው ዝውውር ለመኖሩ መረጃ ላይሆን ይችላል።

ሕግ አስከባሪ ከሆናችሁ አንድ ምርመራ ላይ በጋራ ለመሥራት ወይም ጥቆማ ለማድረግ የ Homeland Security Investigations’ (HSI) መስክ ቢሮን ወይም በአካባቢያችሁ የሚገኘውን Human Trafficking Task Force ተገናኙ። HSI የሰው ዝውውርን የመመርመርና አዘዋዋሪዎችን በቁጥጥር ሥር የማዋል ኃላፊነት አለበት። ተቆጣጣሪያችሁን ለማሳወቅና ተገቢውን የአካባቢ ሥልጣን ለማሳተፍ መከተል ያለባችሁ ድርጅቱ ያወጣው ልዩ የአሠራር ሥርዓት ሊኖር ይችላል። ፈጥኖ ደራሽ ከሆናችሁ እባክዎን ጥቆማ አቅርቡ። የእናንተም ሆነ የተጠቂው ደህንነት መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ሕግ አስከባሪ ካልሆናችሁ በስተቀር፣ መቼም ቢሆን የተጠረጠረን አዘዋዋሪ አትጋፈጡ፣ ተጠቂንም ጥርጣሬያችሁን በተመለከተ አታሳውቁ።

### የሥራ ወይም የአገልግሎት ምልክቶች

- ግለሰቡ ለአንድ ሥራ ተመልምሎ ሌላ ሥራ እንዲሠራ አስገድደውታል?
- ዕዳ ለመክፈል ከግለሰቡ ደምወዝ በቀጥታ ገንዘብ እየተወሰደ ነው?
- ግለሰቡ የግብረሥጋ ድርጊቶች እንዲፈጽም ተገድዷል? ግለሰቡ ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ በጋለሞታነት የተገደደ ሰው ነው?
- ግለሰቡ ከመጠን በላይ ረጅም የሥራ ሰዓት እና/ወይም ከመደበኛ ሰዓት ውጪ የሆነ የሥራ ሰዓት አለው?
- ግለሰቡ ለሚሠራው ሥራ በአግባቡ አልለበሰም?

### የቁጥጥር ምልክቶች

- ግለሰቡ መታወቂያና የጉዞ ሰነዶቹ/ቿ በእጁ/ጇ ነው? ካልሆነ በማ እጅ ነው?
- ግለሰቡ ምን ብሎ መልስ መስጠት እንዳለበት የተነገረው ይመስላል? ሁኔታውን የሚቆጣጠር ከሚመስል ሰው ጋር ነው አብረው ያሉት?
- ግለሰቡ ወይም ቤተሰባቸው ጉዳት ይደርስባችኋል ብሎ ያስፈራራቸው ሰው አለ?
- ግለሰቡ ፈሪ፣ ዝምተኛ ወይም ተገዢ ይመስላል?
- ግለሰቡ/ቧ ከአገር ትባረራለህ/ትባረሪያለሽ ወይም ሕግ አስከባሪ ይጠራብሃል/ይጠራብሻል ብሎ ያስፈራራው/ያስፈራራት አለ?
- ግለሰቡ ግራ የገባው፣ የፈራ ይመስላል? ወይም የአእምሮ ወይም የሰውነት ጉዳት የደረሰበት ይመስላል?
- ግለሰቡ እንደልቡ ጓደኞችን ወይም ቤተሰቦችን ማግኘት ይችላል?
- ግለሰቡ እንደልቡ ሰው ማግኘት ወይም የአምልኮ ቦታ መሄድ ይችላል?

### የኑሮ ሁኔታ ምልክቶች

- ግለሰቡ የግል ንብረት የለውም ወይም የተረጋጋ የኑሮ ሁኔታ የሌለው ይመስላል?
- ግለሰቡ የመንቀሳቀስ ነጻነት አለው? ግለሰቡ ከሚኖርበት ቦታ በነጻነት መሄድ ይችላል? አግባብ የሌላቸው የጥበቃ ሁኔታዎች አሉ?
- ግለሰቡ ምግብ፣ ውሃ፣ እንቅልፍ፣ ሕክምና ወይም ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች አጥቷል?

### የመንገድ ምልክቶች

- ግለሰቡ መድረሻ ቦታውን ያውቃል? በምን መንገድ እንደሚደርስስ ያውቃል?
- መድረሻ ቦታው ላይ ግለሰቡ የሚቀበለውን ሰው ያውቃል?
- ወላጁ ወይም አሳዳጊው ከማይመስል ሰው ጋር የሚጓዝ ልጅ አለ?

### የሕክምና ምልክቶች

- ግለሰቡ ጠባሳዎች፣ የተቃጠለ ቦታ፣ የተቆራረጠ ቦታ ወይም ኢንፌክሽን አለበት?
- ግለሰቡ ስለ ሕክምና ታሪኩ ሲገልጽ ሙሉ በሙሉ እንዳይገልጽ ወይም ጭራሽ እንዳይገልጽ የሚይዘው ነገር አለ?
- ግለሰቡ የሽንት ችግሮች፣ የማህጸን ሕመም፣ እርግዝና ወይም የፊንጢጣ ጉዳት አለበት?
- ግለሰቡ የቆየ የጀርባ፣ የማዳመጥ፣ የልብ ወይም የመተንፈስ ሕመም አለበት?
- ግለሰቡ ዓይኑ በደንብ አያይም ወይም የአይን ችግሮች አሉበት?
- ግለሰቡ ምግብ በደንብ የማይመገብ ወይም ከፍተኛ የጥርስ ችግር አለበት?

BLUE CAMPAIGN
One Voice. One Mission. End Human Trafficking.